# የመቋጫ መልስ ለምሁሩ
# ፕሮ. መስፍን ወ/ማርያምና ለጭፍን ጀሌዎቻቸው !

የስድብ ዓይነቶች የታጨቁበትን የ"ፕሮ." ሊ.ጠ. መስፍንን አጭር የስድብ ጽሑፍ ዓየሁት፡፡ መቸስ በጣም የሚገርም ነው! ከሳቸው ደግሞ ማን ገረመኝ መሰላቹህ ሰውን ተሳደበ እያሉ እራሳቸውን የሥነምግባርና የግብረገብነት መለኪያ አድርገው ሲያወግዙ የሚውሉት ጀሌዎቻቸው ይሄንን የሰውየውን የስድብ ጽሑፍ እየተጋሩ በየግል የፌስ ቡክ አካውንታቸው (የመጽሐፈ ገጽ መዝገባቸው) መለጠፋቸው ነው የገረመኝ፡፡

እኛ ሰውየውን ብንሳደብ ግለሰብ ነው የሰደብነው ያውም በዋሉበት ግብራቸው ወይም ጥፋታቸው፡፡ ሰውየው እኮ ሁሌም የሚሳደበው እንዳለ አንድን ነገድ ወይም ብሔረሰብ ነው፣ መብቱን የጠየቀን ትውልድ ነው፡፡ አፈሩ ይቅለላቸውና ፕሮፌሰር (ሊቀ ጠበብት) ዐሥራት እንኳ አልቀሯቸውም ባሕላችንን በሚጻረር መልኩ ሲዘልፏቸውና ሲያዋርዷቸው፡፡ እና እኒህ ሰው ናቸው ታዲያ "አሳዳጊ የበደላቸው... !" ምንትስ ምንትስ እያሉ ትውልድ የመስደብ የሞራል (የቅስም) ብቃት የሚኖራቸው???

ሰውየ ሆይ! የባለጌ፣ የስድ አደግ፣ የአሳዳጊ የበደለውን ሰው ጠባይና መገለጫ ካወቁና ጨዋ ነኝ ካሉ ታዲያ ምነው በመሳደባችን ያውም በጥፋትዎ ምክንያት ባለጌ አሳዳጊ የበደለው.... ካሉን ሰዎች ጠባይና መገለጫ እራስዎን መጠበቅ ተሳነዎት??? ራስዎትን እየሰደቡ፣ እያዋረዱ፣ በራስዎ ላይ እየመሰከሩ እንደሆነ አልገባዎትም እንዴ??? ከዚህች ቀላል ትዝብት እንኳ እራስዎን መጠበቅ መጠንቀቅ ሳይችሉና መጠንቀቅ እንዳለብዎትም ሳያውቁ ሳይገነዘቡ ነው እንዴ እራስዎን እንደሊቅና ጨዋ (የጠባይ) የሚቆጥሩት??? ለተፈጸመ ጥቃት ተመጣጣኝ የሆነ መልስ የመስጠትና እራስን የመከላከል መብትን ሕግ ደንግጓልና እየሰደቡ፣ እያዋረዱ፣ እየተዳፈሩ ሲጽፉ እየተሰደቡ፣ እየተዋረዱ፣ እየተደፈሩ ይመለስልዎታል፡፡

ዛሬ በሌለ ምሁርነት የተነፋ ትዕቢትዎን ሳላስተነፍሰው አልለቅዎትምና፣ ድንቁርናዎትን ቁልጭ አድርጌ አሳይዎታለሁና ከዚህ በሽታዎ ለመገላገል በተዘጋጀ ልቦና ልብ ብለው ያድምጡኝ! በሚገባ አስተምርዎታለሁ፡፡ የምለው አልገባዎት ብሎ እንደገና "አማራ የሚባል ነገድ ወይም ብሔረሰብ የለም!" ምንትስ ሲሉ ብሰማዎት እጅግ አዝንብዎታለሁና ልብ ብለው ያድምጡኝ፡፡

"እኔ አማራ የለም አላልሁም የትም ቦታ አላልሁም ፤ ያልሁት አማራ የሚባል ጎሣ የለም ነው ያልኩት!" ብለዋል፡፡ አንዱና ትልቁ ድንቁርናዎ ይሄ ነው፡፡ እውነት ነው አማራ (ክርስቲያን) መኖሩን ከደው አያውቁም፡፡ የካዱት አማራ የሚባል በርስዎ አገላለጽ ጎሳ መኖሩን ነው፡፡ ሲጀመር አማራ ጎሳ አይደለም እሽ ጋሽ መስፍን??? ጎሳ ማለት በማኅበረሰብ አደረጃጀት ከቤተዘመድ ከፍ ብሎ የሚገኝ አደረጃጀት ነው፡፡ አደረጃጀቱ እንዴት መሰለዎት መጀመሪያ ላይ ግለሰብ አለ ከዛ ቤተሰብ አለ ከዚያ ቤተዘመድ አለ ከዚያ ጎሳ አለ ከዚያ ነገድ አለ ከዚያ መጨረሻ ላይ ሕዝብ አለ፡፡ በዘልማድ ግን ብሔረሰብ ከጎሳ ከፍ ላለ የማኅበረሰብ አደረጃጀት በነገድ ምትክ እንጠቀማለን ነገር ግን ስሕተት ነው፡፡ ብሔረሰብ ማለት የሰው ሀገር ማለት ነው ወደ አማርኛ ሲመለስ፡፡ ብሔር ማለት ደግሞ ሀገር ማለት እንጅ የማኅበረሰብ አደረጃጀት አይደለም፡፡

ነገድን ከ 12 ቱ የያዕቆብ ልጆች ከወጡት የእስራኤል (የያዕቆብ) ዘሮች ጋር በማያያዝ አሳንሰን እንዳናስበው እንጠንቀቅ፡፡ ምክንያቱም የእስራኤል (የያዕቆብ) ልጆች በነገድ የመሠየም ምክንያቱ "ዘርህን እንደሰማይ ከዋክብት እንደምድር አሸዋ አበዛዋለሁ....!" የሚለውን ቃልኪዳን ታሳቢ ያደረገ ነውና፡፡ ሕዝብ ስንልም ምን ማለታችን እንደሆነ አገባቡ ነው የሚወስነው፡፡ በምድራችን ያለውን የሰው ልጅ ሁሉ የዓለም ሕዝብ ልንል እንችላለን፣ የአንድ ሀገርን ሰዎች ሕዝብ ልንል እንችላለን፣ ከነገድ ከፍ ላለ የማኅበረሰብ አደረጃጀት ለበቃ ማኅበረሰብ ሕዝብ ልንል እንችላለን፡፡ ለእነኝህ የማኅበረሰብ አደረጃጀቶች ብየና ቁጥርና አሐዳዊነት ወይም መመሳሰል (በባሕል፣ በቋንቋ፣ በአስተሳሰብ፣ በጋራ ጥቅም ወዘተረፈ.) ዋነኛ መስፈርቶች ናቸው፡፡

እንግዲህ እስርዎ አማራን ጎሳ ሲሉት ምን ያህል እንዳሳነሱት የሚገባዎት ይመስለኛል፡፡ ሆን ብለው አማራን ለማሳነስ በማሰብ ካልሆነ አማራን ጎሳ እያሉ ያሉት ይሄ ድንቁርናዎትን ያሳያል፡፡

አሁን በቋንቋ በባሕል ... የተለያዩ ነገዶች ወይም በዘልማድ ብሔረሰቦች የምንላቸው ማኅበረሰባዊ አደረጃጀቶች እንዴት እንደሚፈጠሩ ዕንይ፦

ጎሳ በአንድ ነገድ ወይም በዘልማድ ብሔረሰብ በምንለው ማኅበረሰባዊ አደረጃጀት ውስጥ የምናገኘው ማኅበረሰባዊ አደረጃጀት ተመሳሳይ ቋንቋ ባሕል... ያላቸው ቡድኖች ናቸው፡፡ በአነስተኛ በአነስተኛ ቁጥር ያሉ ተመሳሳይ ቋንቋ፣ ባሕል... ያላቸው የተለያዩ ቡድኖችም የጎሳ አጀረጃጀት ደረጃ ይኖራቸዋል፡፡

ወደ ነገድ ወይም በዘልማድ ብሔረሰብ ወደምንለው ስናልፍ፡- በነገድ አደረጃጀት ውስጥ በተለያዩ ነገዶች መሀከል ተመሳሳይ ቋንቋ ባሕል... የሚጠበቅ አይደለም፡፡ አንድ ጎሳ ቁጥሩ ሳያድግና የራሱን ቋንቋ ባሕል... ሳይይዝ፣ ሳያዳብር ሳይፈጥር ነገድ የመሆን ብቃት አይኖረውም፡፡ ከአንድ ነገድ ውስጥ ሌላ ነገድ የሚወጣውም ወይም የሚፈጠረውም በዚሁ መንገድ ነው፡፡ በአንድም በሌላም ምክንያት አንድ ቡድን ከነበረበት ነገድ የተለየ ቋንቋ ባሕል...ሲፈጥር አዲስ ጎሳ ሆኖ ይወጣል፡፡ ጎሳ ሆኖ ለመውጣት ግን አዲስ ቋንቋ ባሕል... ይዞ መገኘት የግድ አይደለም፡፡ ጎሳው አዲስ የራሱን ቋንቋ ባሕል... ሲያዳብርና ቁጥሩ ከፍተኛ ሲሆንም ወደ ነገድነት ይለወጣል ወይም ነገድ ይሆናል፡፡ ጋሽ መስፍን እንግዲህ በዚህ ሒደት ነው የሰው ልጅ ከአንድ እናትና አባት የተገኘ ሆኖ እያለ ቁጥሩ እያሻቀበ ሲሔድ ጎሳ ነገድ ሕዝብ እየተፈጠሩ መጥተው ዛሬላይ ዓለማችን በበርካታ ጎሳዎችና ነገዶች ብሎም ሕዝቦች ልትሞላ የቻለችው፡፡

ጋሽ መስፍን "የነገድ አደረጃጀት እንዲህ ከሆነ ታዲያ የእስራኤል ልጆች እንዴት በ 12 ነገድ ተቆጠሩ?" ብለው ከጠየቁኝ ልብ ብለው እየተከታተሉኝ አይደለም ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም ከላይ የነገደ እስራኤል በ 12 ነገድ መከፈል ዘራቸው እንደ ሰማይ ከዋክብት እንደ ባሕር አሸዋ የሚበዛ መሆኑን ታሳቢ ያደረገ መሆኑን መናገሬን እረስተውታል ማለት ነው፡፡ በዚህም መሠረት የእስራኤል ዘር እንደጨው ዘር በዓለም ተረጭተው የተለያየ ቋንቋ ባሕል... ማደበራቸውን ልብ ይበሉ፡፡ ቃልኪዳኑም ተፈጽሞ እኛንና ሌሎች አፍሪካውያንን የወሰዱ እንደሆነ፣ ዓረቦችን የወሰዱ እንደሆነ፣ ምዕራባውያኑን የወሰዱ እንደሆነ፣ ምሥራቃውያኑን የወሰዱ እንደሆነ ሁሉም በትውፊታዊ ትርክቱ "የእስራኤል ዘር አለን!" የማይል የለም፡፡ በዚህ ላይ ደግሞ ከብዛታቸው የተናሣ ቁጥር የማይገልጻቸው መላእክት በነገድ የተከፈሉ መሆናቸውን አይዘንጉ፡፡

አሁን ወደ እርስዎ ሌላኛው ድንቁርና ልምጣና የእርስዎ ችግር ወይም አላዋቂነት ምን መሰለዎት እርስዎ በአስተሳሰብዎ ጎሳና ነገድ (ብሔረሰብ) በጥንት ዘመን የሆነ ወቅት ላይ ተፈጥረው የቆሙ እንደሆኑ አድርገው ማሰብዎ ወይም ማመንዎ ነው፡፡ እንደሱ አይደለም እሽ ጋሽ መስፍን??? እንኳን አይደለም ከሽዎች ዓመታትና ከመቶዎች ዓመታት በፊት ይቅርና ከዚህ ዘመን በኋላም ራሱ ከላይ የጠቀስኩልዎት ቅድመ ሁኔታዎች እስከተሟሉላቸውና እስከፈቀዱላቸው ጊዜ ድረስ አዳዲስ ጎሳዎች አዳዲስ ነገዶችና ሕዝቦች ገና ወደፊት ይፈጠራሉ እሽ???

የሰው ልጅ እርባታውና እንቅስቃሴው እስካልቆመ ጊዜ ድረስ አዳዲስ ጎሳዎችና አዳዲስ ነገዶች ብሎም ሕዝቦች መፈጠራቸው የማይቀርና ተፈጥሯዊ ሀቅ ነው እሽ ጋሽ መስፍን? እንጅ በሆነ የጥንት ዘመን ተፈጥረው የቆሙ ማኅበረሰባዊ አደረጃጀቶች አይደሉም፡፡ እንደዛ ብለው በማመንዎም ነው "አማራ የሚባል ነገድ ወይም በዘልማድ ብሔረሰብ ብሎም ሕዝብ የለም!" ለሚል ለተሳሳተ ድምዳሜ ሊዳረጉ የቻሉት፡፡ አሳፋሪ በሆነ የድንቁርና ድርቅና ሽንጥዎን ገትረውም የሚከራከሩት፡፡ ለዚህም ነው ይሄ ተግባርዎ ወንጀልና የሚያስከስስ የሚያስቀጣ የሙብት ጥሰት የሚሆንብሆት፡፡ ጋሽ መስፍን የምልዎት ግን ይገባወታል??? የኤትኖሎጅው ሳይንስ (የሰው ዘሮች ጥናት መጣቅ) የሚለው የገለጽኩልዎትን ነው፡፡

ከላይ በገለጽኩልዎት የነገድ አፈጣጠር መሰረትም የሚያውቁ ከሆነ አማራ የተፈጠረው ከአገው ነው፡፡ አማራ ማለት ከተሜ ወይም የሠለጠነ አገው ማለት ነው፡፡ ከደቡብ ዓረቢያ ፈልሰው የገቡቱ ሳባውያኑ ከእራት ሽህ ዓመታት በፊት ገብተው የተዋሐዷቸው ከተሜ ከተሜ አገዎች ናቸው አማራ ሆነው የወጡት፡፡ በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ መሠረታዊ የሆኑ እነ ሸ፣ ቸ፣ ኘ፣ ኸ፣ ዠ፣ ጀ፣ ጨ ኩሻዊ ድምፆች ሊኖሩ የቻሉት በዚህ ምክንያት ነው፡፡ ከአንድ ሽህ ዓመታት በኋላ ደግሞ አይሁዶቹ መጥተው ተዋሕደውታል፡፡ ባጭሩ አማራ ማለት ይሄ ነው፡፡

አዎ ከሣቴ ብርሃን ተሰማ አማራ ማለት፡- የተመረጠ፣ ነጻነት ያለው፣ አሸናፊ፣ ድልነሽ ሕዝብ ማለት ነው ማለታቸው፡፡ አለቃ ደስታ ተክለ ወልድ፡- ዐም ሕዝብ፣ ሐራ ነጻ በተገናኘ ነጻ ሕዝብ፣ ገዢነት እንጂ ተገዢነት የማይስማማው ሕዝብ ማለት ነው ማለታቸው፡፡ አለቃ ዓጽሜ፡- አማራ ከወዴትም አልመጣም ጥሩ የላስቶች ወታደር፣ከየዓይነቱ የተጠራቀመ፣ ኃይለኛ፣ አድመኛ እውቀት ያለው ሕዝብ ማለት ነው ማለታቸው...... ትክክል ነው፡፡

አማራ ወይም ዐማራ በአልፋው አ እና በዐይኑ ዐ ሲፃፍ የተለያየ ትርጉም እየሰጠ ከላይ የተጠቀሱትን ትርጉሞች ሁሉ ማለት ነው፡፡ በአልፋው አ ሲጻፍ አዋቂ ጠቢብ ሕዝብ የሚለውን ትርጉም ይሰጣል፡፡ አመረ ወይም አንዳንዶቹ አእመረ ብለው ከሚገልጹት ግስ ነው የወጣው ቃሉ፡፡ አንዳንድ ሊቃውንት አእመረ አስደራጊ ግስ ስለሆነ አምዱ አመረ ነው ይላሉ፡፡ በማሳሌ ሲያስረዱም ቀተለ ከሚለው አድራጊ ግስ አቅተለ የሚል አስደራጊ ግስ እንዲገኝ፡፡ በዚህም መሠረት አመረ ከሚል ግስ አእመረ የሚል አስደራጊ ግስ ይገኛል ማለት ነው፡፡ አመረ ማለት አወቀ ማለት ነው፡፡ አመረ ወይም አእመረ የሚለው ግስ ጥሬዘሩ

አማራ ነው፡፡ ስለዚህም ቃሉ በቁሙ ተወስዶ ነው የአማራ ሕዝብ ስም ሊሆን የቻለው፡፡

ጋሽ መስፍን እና እኮ ታዲያ ይሄ የጠቀሱት የሊቃውንቱ ትርጉም የሚጠቅመው እኮ "አማራ የሚባል ሕዝብ፣ ነገድ፣ ዘር አለ!" የምንለውን እኛን ነው እንጅ "አማራ ክርስቲያን ማለት እንጅ የነገድ፣ የዘር፣ የሕዝብ ስም አይደለም!" የሚሉትን እርስዎን ነው እንዴ??? እስኪ ልብ ብለው ይመልከቱት??? ነው ወይስ አማራ የሚለው ቃል የዘር ስም ለመሆን ትርጉም የሌለው መሆን አለበት ነው እያሉ ያሉት??? ሁሉም የዘር ስም እኮ ስሙ የወጣለት በምክንያትና በትርጉም ነው፡፡ ትርጉም የሌለው የጎሳ የነገድና የሕዝብ ስም አለ እንዴ???

ለምሳሌ ኦሮሞ የሚለውን ስም ያወጣው በ 19 ኛው መቶ ክ/ዘ ጀርመናዊው ሉተራዊ የቅኝ ግዛት ሰላይ ሚሽነሪ (መልእክተኛ) ዮሐን ክራፍ ነው፡፡ ዮሐን "ጋላ ማለት ስደተኛ ማለት ነውና ሌላ ስም ያስፈልጋቹሀል!" ብሎ ነው "ጋሎችን ከያዝን ምሥራቅና መካከለኛው አፍሪካን ያዝን ማለት ነው!" ብሎ ያምን ስለነበረ የኦሮሞን ሕዝብ በመያዝ ምሥራቅና መካከለኛው አፍሪካን የጀርመን ቅኝ ግዛት ለማድረግ ሲል በስም ለመደለል ሕዝቡን ኦርማ ወይም ኦሮማ ብሎ በመሠየም ከኢትዮጵያ ገንጥሎ መውሰድ የፈለገውን የሀገራችንን ክፍል ደግሞ ኦርማንያ የሚል ስም አውጥቶ የጀርመን ቅኝ ግዛት ለማድረግ ይጥር እንደነበረ ታሪኩ ያስረዳል፡፡ በሒደት ኦሮሞና ኦሮሚያ የሚል ቃል አወጡ፡፡

በነገራችን ላይ ጋላ ማለት ኦሮሞ ማለት አይደለም፡፡ በግእዝ መጻሕፍት አተረጓጎም መሠረት ጋላ ማለት ያላመነ ያልተጠመቀ አረማዊ የሚል ትርጉም ከሚሰጡ ቃላት አንዱ ነው እንጅ የጎሳ ወይም የነገድ ስም አይደለም፡፡ ለዚህም ማስረጃው ዛሬ ሊቢያ ብለን በምንጠራት ሰሜን አፍሪካዊት ሀገር ከሀዲው አርዮስ ተፍጻሜተ ሠማዕት ቅዱስ ጴጥሮስን በጋላ አንገቱን አስቆርጦ እንዳስገደለው የግእዝ መጻሕፍት ይናገራሉ፡፡ እስላሞች ግብጽን ሲወሩ ያፈረሷቸውን አብያተክርስቲያናትን ጋሎች በማለት እንዳፈረሷቸው ይናገራሉ፡፡ በመሆኑም ጋላ ማለት የአንድ ጎሳ ስም ሳይሆን ያላመነ ያልተጠመቀ አረማዊ የሆነ ሕዝብ ከሚጠራባቸው ቃላት አንዱ ነው እንጅ ኦሮሞ ማለት አይደለም፡፡

ጉራጌ የሚለው ስም ለጉራጌዎች የወጣው ዛሬ ኤርትራ ተብላ ከምትጠራው የሀገራችን ክፍል ጉርአ ተብሎ ከሚጠራው ሥፍራ የመጡ ስለሆኑ ከቦታው ስም የተነሣ የጎንደርን ሰው ጎንደሬ እንዲሉት የጉርአ ሰው ስለሆኑ ጉራጌ እንደተባሉ አለቃ ታዬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ በሚለው መጽሐፋቸው ሌሎችም እንዲሁ ይናገራሉ፡፡

ትግሬ የሚለው ስምም እንዲሁ ትርጉም አለው፡፡ በእግር የሚረገጥ ወይም ተረጋጭ (ተገዥ፣ አገልጋይ፣ ባሪያ) ማለት ነው፡፡ ለዚህም ነው ትግሮቹ ትግሬ ተብለው መጠራት የማይፈልጉትና ቃሉን የሚሸሹበት ምክንያት፡፡ ሳስበው እንዲያውም ጋሽ መስፍን በዚህ ትግሬ በሚለው ስም ቅሬታ ሳይሆን አይቀርም "አማራ የለም!" እያሉን ያሉት፡፡ ለማንኛውም ትርጉም የሌለው የዘር፣ የጎሳ፣ የነገድ፣ የሕዝብ ስም የለም፡፡ ቃሉ ትርጉም ስላለው የዘር የነገድ የሕዝብ ስም አይደለም ወይም አይሆንም የሚባል ነገር አይተንም ሰምተንም አናውቅምና "አማራ ማለት ..... ማለት ስለሆነ የዘር ስም አይደለም!" የሚለው የመከራከሪያ ነጥብዎ ውኃ የሚቋጥር አይደለም እሽ ጋሽ መስፍን???

ከሰሞኑ ጽፈውት ወደነበረው  ጽሑፍዎ ልመለስና የጠቀሱትን ነጥብ ላንሣ "... ስለጎሣ ማወቅና መረዳት የፈለጉ በጎሣነት የታወቁ ማኅበረሰቦች እያንዳንዳቸው አባሎቹን ሁሉ የሚያያይዛቸው የጋራ መሪ እንዳላቸው መገንዘብ፣ በዘፈናቸው፣ በስክስታቸው፣ በምግባቸውና በመጠጣቸው፣ በልብሳቸው ... መመሳሰል እንዳሉባቸው ማወቅ ይጠቅማል፡፡ መረጃንና ማስረጃን ለመቀበል ለሚችል አእምሮ በተዘረዘሩት ላይ ጠለቅ እያሉ በማሰብ የአስተሳሰብ ጉድፍን ለማጥራት ይቻላል!" ይላል ሐሳብዎ፡፡ በጣም የሚገርም ነው ምክንያቱም ብየናዎት በጣም ያልበሰለ በመሆኑ ነው፡፡ አማራ የጎሳ መሪ የሌለው ከላይ ለመግለጥ እንደሞከርኩት ከጎሳነት ያለፈና ነገድ በመሆኑ ነው እሽ???

"በዘፈናቸው፣ በስክስታቸው፣ በምግባቸውና በመጠጣቸው፣ በልብሳቸው ... መመሳሰል እንዳሉባቸው ማወቅ ይጠቅማል!" ላሉት ግን ያልጠቀሱትን ቋንቋንና ባሕልን ልጨምርና አማራ ተመሳሳይ ዘፈን፣ እስክስታ፣ ምግብና መጠጥ፣ ልብስ፣ ባሕል፣ ቋንቋ እንዳለው አያውቁም እንዴ ጋሽ መስፍን??? ይሄንን አያውቁም ማለት እኮ ጨርሶ ምንም ግንዛቤው በሌለዎት ጉዳይ ነው እየዘባረቁብን ያሉት ማለት እኮነው! ይሄ አያሳፍርዎትም??? እኔ እርስዎን ቢያደርገኝ በዚህ የድንቁርና ቅሌቴ ሀገር ጥየ እጠፋ ነበረ ወይም ደግሞ እራሴን አጠፋ ነበረ፡፡ እንዲያው እፍረት የሚባል ነገር ጥቂት እንኳ አልፈጠረብዎትም ባዶ ሆነው እያለ እንዲህ እራስዎትን እንደ ሊቅ ቆጥረው ለመታበይ ሲዳዳዎት???

እኛ እኮ እንዲያውም ጠባብ የኦሮሞ ብሔርተኞችና መሰሎቻቸው ምን እያሉ እንደሚያሙን አልሰሙም እንዴ? "አማራ ባሕሉን፣ ቋንቋውን፣ ልብሱን፣ ምግቡንና መጠጡን፣ ዘፈኑን... ጭኖብናል!" እኮነው እየተባልን እየተከሰስን ያለነው፡፡ እርስዎ ደሞ በዚህ በኩል በምን ዓይንዎት ለማየት እንደሞከሩ አላውቅም "የጎሳ መሪና ተመሳሳይ ዘፈን፣ እስክስታ፣ ምግብና መጠጥ፣

ልብስ ... ያለው አማራ የሚባል ጎሳ የለም!" ይላሉ፡፡ ግን የጤና ነው??? ለመሆኑ እንዲህ ግትርና ምክኒያታዊነት በራቀው ሰብእናዎት እንዴት ሆነው ተምረው ነው ግን ጭራሽ ፕሮፌሰር ለመባል የበቁት??? ነው ወይስ በዚያ ዘመንም ዲግሪ ይገዛ ነበረ??? ስለ እርስዎ ሳስብ ግርም የሚለኝ ነገር ቢኖር ይሄ ነው፡፡

ጭራሽ ደንቆሮ፣ ድንጋይ ራስ፣ ፊደላውያን ምንትስ ምንትስ ተብሎ ይሰደብልኛል እንጅ፡፡ ሲጀመር ፊደላውያን (Alphabetics) የሚለውን ቃል ለስድብነት የተጠቀመው ስሙን ለጊዜው የዘነጋሁት ታንዛኒያዊ ምሁር ነው መጽሐፉ ላይ ቃሉን የተጠቀመው፡፡ እሱ ቃሉን የተጠቀመበት እርስዎ እንዳሉት ፊደልን በመከራ ተምረው ፊደል ስላወቁ የተማሩ የሚመስላቸውን ሳይሆን ፒኤችዲ ይዘው ወይም ዶክተር (ሊቀ ማእምራን) ተብለው ፣ ፕሮፌሰር (ሊቀ ጠበብት) ተብለው ልማዳዊ አስተሳሰብ ወይም መንገድ የሚሔዱትን፣ እንደርስዎ ፈጦ የሚታይ እውነታን ማየት መረዳት መገንዘብ የማይችሉትን፣ በተለየ መንገድ ማሰብ የማይችሉትን የምሁር መሐይምናንን ነው አልፋቤቲክስ (ፊደላውያን) ሲል በመጽሐፉ የጠራቸው፡፡

እስኪ አንድ ጥያቄ ልጠይቅዎት ጋሽ መስፍን "አማራ ማለት ክርስቲያን ማለት ነው እንጅ የዘር ስም አይደለም!" ብለዋል፡፡ አዎ ልክ ነዎት አማራ ማለት ከዘር ስምነት በተጨማሪ ክርስቲያን ማለት ነው፡፡ ባይገርምዎት ይሄ አባባል የሚያረጋግጠው አማራ የሚባል ዘር ነገድ ሕዝብ መኖሩን ነው፡፡ እንደሚያውቁት በሌሎች ሀገራት ክርስቲያን ክርስቲያን ይባላል እንጅ አማራ ተብሎ አይጠራም፡፡ እንዲህ ከሆነ ታዲያ በሀገራችን ለምንና እንዴት ክርስቲያን አማራ ሊባል የቻለ ይመስልዎታል??? ይሄንን ሊመልሱ ይችላሉ??? በእርግጠኝነት አይችሉም!!! ምክንያቱም ይሄንን ጥያቄ መመለስ ቢችሉ ኖሮ በፍጹም "አማራ የሚባል ዘር የለም!" ሊሉ አይችሉም ነበርና ነው፡፡

መልሱን እኔው እዚሁ እሰጥዎታለሁ፡-

ኢትዮጵያ ውስጥ ክርስትና ቀድሞ የገባው በሐዋ. 8፣26-40 ላይ እንደሚያነቡት በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ በባኮስ በኩል እንዲሁም በአራተኛው መቶ ክ/ዘ በአቡነ ፍሬምናጦስ ከሳቴ ብርሃን በኩል ቀጥታ ወደ ቤተመንግሥቱ ስለሆነና ከቤተመንግሥቱ ወደ ሕዝቡ ስለሆነ የወረደው ወይም የተስፋፋው የእምነቱ ስም በንጉሣውያኑ ዘር ወይም ነገድ ስም ሊጠራና አማራ ሊባል ቻለ፡፡

በዘመኑ ክርስትና ብሔራዊ ሃይማኖት ተደርጎ መታወጁ በፈጠረው አለመግባባት በአይሁዶቹ እና በክርስቲያኑ (በአማራው ወይም በአክሱማውያኑ) መሀከል ግጭት ተፈጥሮ እስከ ዘጠነኛው መቶ ክ/ዘ ድረስ በግጭቶች ቆይተው በዘጠነኛው መቶ ክ/ዘ ላይ ግን በዮዲት ጉዲት ዘመን (842-882 ዓ.ም.) አይሁዶቹ ድል ቀንቷቸው ለማሸነፍ በቅተው ቀደምቱን የአይሁድነት እምነት ትተው ክርስትናን ብሔራዊ ሃይማኖት አድርገው ያወጁቱ አማሮቹ ወይም አክሱማውያኑ በዮዲት ጉዲት ጦር ለ 40 ዓመታት በተወሰደበት አማራን የማጥፋት እርምጃ አማሮች ከአክሱም ተመንጥረው ለመጥፋት ምክንያት ሆኗል፡፡ ባጭሩ ክርስትና አማራ የመባሉ ምክንያት ይሄው ነው እሽ ጋሽ መስፍን???

እንግዲህ በተቻለኝ መጠን በችኮላም ቢሆን የጻፍኩት ይሄ ጽሑፍ ያለብዎትን ብዥታ ያጠራልዎታል፣ ያለብዎትን የዕውቀት ክፍተት ጥግብ አድርጎ ይሞላልዎታል ብየ አምናለሁ፡፡ ግድ የለዎትም ፕሮፌሰርም ከገበሬ ሊማረው የሚችለው ብዙ የማያውቀው ነገር አለና "እኔ ባንተ እንዴት እማራለሁ?" ብለው ሳይንቁኝ የሰጠሁዎትን ትምህርት ይውሰዱ እሽ??? በዚህ ከተስማማን ከዚህ በኋላ "አማራ የሚባል ዘር የለም!" የሚባል ነገር ከአንደበትዎ እንደማይወጣ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ነገር ግን "አይ!" ብለው ከዚህም በኋላ የሚቀጥሉ ከሆነ ግን አልዋሸዎትም እርስዎን "ምንም መረዳት የማይችል፣ የማይገባው ሰው!" የሚለውን ይተውትና ጨርሶም እንደጤነኛ ሰው ለማየት እንደሚሳነኝ ከወዲሁ ልገልጥልዎ እወዳለሁ፡፡ መድኃኔዓለም ክርስቶስ አእምሮውን፣ ልቡናውን፣ ማስተዋሉን ይስጥዎት!!!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!
ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!
ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው
amsalugkidan@gmail.com

http://www.ethiopanorama.com/?p=74849